# የድህነታችን ገፅታና ትምህርት የሚጠበቅበት ድርሻ*

ተሾመ ይዘንጋው**

## ሀገራችን ያለችበት ሁኔታ ምን ይመስላል?

### *ኢኮኖሚውና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ*

ኢትዮጵያ በልማት በዓለም ላይ በጣም ወደኋላ ከቀሩት ሃገሮች አንዷና የመጨረሻዋ ዲሞክራሲያዊ ባህልና ሥርዓት በመገንባት ረገድም ገና ጀማሪ በመሆንዋ ፀረ ዲሞክራሲያዊ የሆኑ አስተሳሰቦችና አሰራሮች ከፍተኛ ቦታ በመያዝ ያለውንም ጅምር በየጊዜው ወደኋላ በመጎተት ላይ ይገኛሉ።

ስለዚህ ያለንበት ሁኔታ እጅግ በከፋ የድህነትና በልማት ኋላቀርነት እንዲሁም ዲሞክራሲያዊ ባህል ገና ባልተገነባበትና ጅምሩም ብዙ ፈተና ባለበት ወቅት ነው። በፖለቲካው መስክ የብሄር ብሄረሰቦችን መብቶችና የዜጎችን ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች የማስከበር መርሆዎችና የህግ የበላይነት በየአጋጣሚው የሚሸረሸሩበት ሁኔታ ይታያል። ልዩነቶችን በሰላማዊና በመተማመን የመፍታትን አካሄድ አለመከተል በእርስ በእርስ ግንኙነት እና በዕለት ተዕለት ስራችን ዲሞክራሲያዊ ባህልን አለማዳበር ወዘተ በሰፊው ይስተዋላሉ። በኢኮኖሚና ማኅበራዊ መስክ ዜጎች የመሰረተ ልማት /መንገድ፥ ውሃ፥ መብራት፥ ቴሌፎን ወዘተ/፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የፍትህ፥ የግብርና ግብዓቶች፥ ወዘተ አገልግሎቶችን በበቂ አላገኙም፣ በብዙ አካባቢዎችም አገልግሎቶቹ የሉም ለማለትም ያስደፍራል። ይህንን ሁላችንም በጥልቀት ተረድተናል ማለት የሚያስደፍር በመሆኑ የድህነታችንን መጠንና ያለንበትን ደረጃ በአግባቡ መረዳት ያስፈልገናል።

ከዚህ አስከፊ ድህነት በመውጣት፥ ዲሞክራሲያዊ ባህል የተገነባበትና የበለጸገ ህብረተሰብ እንዲኖረን ማድረግ መቻል ያለብን ሲሆን በዚህ ረገድ የተማረው ክፍል ሚና ወሳኝ ነው። እነዚህ ለውጦችና ዕድገቶችም መምጣት ያለባቸው በጣም በፈጠነ መንገድ መሆን ስላለበት በአጭር ጊዜ ውስጥ (20 - 30 ዓመታት) ከድህነት ለመውጣት መጣርም፥ መቻልም አለብን። ይህ ፈጣን ዕድገት የሚቻል እንደሆነ እምነት ሊኖረን ይገባል፣

---

* ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሃላፊዎች ጋር ከየካቲት 18-21 1995 ዓ.ም. በተደረገ የምክክር ስብሰባ ላይ የቀረበ ፅሁፍ

** Ph.d; ምክትል ሚኒስትር፣ ትምህርት ሚኒስቴር

# የድህነታችን ገፅታና ትምህርት የሚጠበቅበት ድርሻ*

ተሾመ ይዘንጋው**

## ሀገራችን ያለችበት ሁኔታ ምን ይመስላል?

### *ኢኮኖሚውና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ*

ኢትዮጵያ በልማት በዓለም ላይ በጣም ወደኋላ ከቀሩት ሃገሮች አንዷና የመጨረሻዋ ዲሞክራሲያዊ ባህልና ሥርዓት በመገንባት ረገድም ገና ጀማሪ በመሆንዋ ፀረ ዲሞክራሲያዊ የሆኑ አስተሳሰቦችና አሰራሮች ከፍተኛ ቦታ በመያዝ ያለውንም ጅምር በየጊዜው ወደኋላ በመጎተት ላይ ይገኛሉ።

ስለዚህ ያለንበት ሁኔታ እጅግ በከፋ የድህነትና በልማት ኋላቀርነት እንዲሁም ዲሞክራሲያዊ ባህል ገና ባልተገነባበትና ጅምሩም ብዙ ፈተና ባለበት ወቅት ነው። በፖለቲካው መስክ የብሄር ብሄረሰቦችን መብቶችና የዜጎችን ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች የማስከበር መርሆዎችና የህግ የበላይነት በየአጋጣሚው የሚሸረሸሩበት ሁኔታ ይታያል። ልዩነቶችን በሰላማዊና በመተማመን የመፍታትን አካሄድ አለመከተል በእርስ በእርስ ግንኙነት እና በዕለት ተዕለት ስራችን ዲሞክራሲያዊ ባህልን አለማዳበር ወዘተ በሰፊው ይስተዋላሉ። በኢኮኖሚና ማኅበራዊ መስክ ዜጎች የመሰረተ ልማት /መንገድ፥ ውሃ፥ መብራት፥ ቴሌፎን ወዘተ/፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የፍትህ፥ የግብርና ግብዓቶች፥ ወዘተ አገልግሎቶችን በበቂ አላገኙም፣ በብዙ አካባቢዎችም አገልግሎቶቹ የሉም ለማለትም ያስደፍራል። ይህንን ሁላችንም በጥልቀት ተረድተናል ማለት የሚያስደፍር በመሆኑ የድህነታችንን መጠንና ያለንበትን ደረጃ በአግባቡ መረዳት ያስፈልገናል።

ከዚህ አስከፊ ድህነት በመውጣት፥ ዲሞክራሲያዊ ባህል የተገነባበትና የበለጸገ ህብረተሰብ እንዲኖረን ማድረግ መቻል ያለብን ሲሆን በዚህ ረገድ የተማረው ክፍል ሚና ወሳኝ ነው። እነዚህ ለውጦችና ዕድገቶችም መምጣት ያለባቸው በጣም በፈጠነ መንገድ መሆን ስላለበት በአጭር ጊዜ ውስጥ (20 - 30 ዓመታት) ከድህነት ለመውጣት መጣርም፣ መቻልም አለብን። ይህ ፈጣን ዕድገት የሚቻል እንደሆነ እምነት ሊኖረን ይገባል፣

---

* ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሃላፊዎች ጋር ከየካቲት 18-21 1995 ዓ.ም. በተደረገ የምክክር ስብሰባ ላይ የቀረበ ፅሁፍ

** Ph.d; ምክትል ሚኒስትር፣ ትምህርት ሚኒስቴር

የሌሎች ሃገሮችም ተመክሮ እንደሚቻል ያስተምረናል። ለውጥንና ዕድገትን ከማስመዝገብ አንፃር ባለፉት አስር ዓመታት የተሰሩ ስራዎችን ብንመዝን በጣም በርካታና ሰፋፊ ተግባራት ተከናውነዋል። በመሰረተ ልማት ግንባታ፣ በማኅበራዊ አገልግሎቶች ማስፋፋት፥ እንዲሁም በኢኮኖሚያዊ ልማት ረገድ የማይናቁ ውጤቶች ተመዝግበዋል (ሰንጠረዥ 1)።

ሰንጠረዥ 1: **የተለያዩ የመሰረተ ልማትና ማኅበራዊ አገልግሎቶች ዕድገት**

| ተግባራት | | እስከ 1983 | 1983-1994 |
|---|---|---|---|
| መንገድ | ጠቅላላ | 19,017 ኪ.ሜ | 33,297 ኪ.ሜ. |
| | አስፋልት | 4,109 | 4,053 |
| | ጠጠር | 14,908 | 29,244 |
| ስልክ | መስመር | 171,182 | 669,817 |
| | የተጠቃሚ ብዛት | 136,945 | 385,800 |
| | ሞባይል አቅም | - | 60,000 |
| | የሞባይል ተጠቃሚ ብዛት | - | 52,283 |
| | ኢንተርኔት አቅም | - | 14,000 |
| | የኢንተርኔት ተጠቃሚ ብዛት | - | 8,511 |
| ኢሌክትሪክ | ማመንጨት አቅም | 355 ሜጋ ዋት | 520.3 ሜጋ ዋት |
| | ማስተላለፊያ መስመር | 9,887 ኪ.ሜ | 19,323 ኪ.ሜ. |
| | የተጠቃሚ ህዝብ ብዛት | 5,053,000 | 10,017,000 |
| ጤና | ሽፋን (የመንግስት) | 32% | 61% |
| | ሌሎች ጨምሮ | - | 70.7% |
| ትምህርት | 1-6 ክፍል | 20% | 70% |
| | ተማሪ ብዛት | 1.8 ሚ. | 8.7 ሚ. |
| | ከፍተኛ ትም/ቅበላ | 6 ሺህ | 18 ሺህ |
| | የሙያና ቴክኒክ ትም/ቅበላ | 800 | 25 ሺህ |

*ምንጭ፦ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙዩኒኬሽን ኮርፖሬሽን፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የትምህርት ሚኒስቴር

ከላይ በሰንጠረዡ እንደተቀመጠው በተለይ ባለፉት አስር ዓመታት መንገድ፥ ስልክና ኤሌክትሪክን የመሳሰሉ የመሰረተ ልማት አውታሮች በከፍተኛ ደረጃ አድገዋል በማህበራዊ ዘርፍም የጤናና የትምህርት ሽፋን ከፍተኛ እድገት አሳይተዋል። ይህ የሚያመላክተን አንድ ቁምነገር አሁን እየሄድንበት ባለነውና በምንም ደረጃ በቂ ነው በማይባለው አሰራርና ፍጥነታችንም ቢሆን ዕድገትና ለውጥ ማምጣት እንደቻልን ነው።

ይሁንና ይህ ከፍተኛ ነው የምንለው ሥራ በህብረተሰባችን የኑሮ ሁኔታ፣ በእያንዳንዱ ዜጋ ህይወትና በአጠቃላይም በሀገሪቱ ዕድገት ላይ ያመጣው ለውጥና ዕድገት ይህ ነው መባል የማይችልና ከድህነት የመጨረሻው መስመር ፈቀቅ ያላደረገን ነው። በየትኛውም የሃገሪቱ ክፍሎች የምናየው የስራ አጥነት እና የጎዳና ተዳዳሪዎች ብዛት፥ የመሰረታዊ ጉዳዮች (ምግብ፣

መጠለያ፥ ልብስ) አለመሟላት፥ እንዲሁም በየዓመቱ እየመጣ ያለውን ድርቅ ለመቋቋም አቅም በማጣት ተመፅዋች መሆን የድህነታችንን ስፋትና ጥልቀት ሊገልፁ የሚችሉ ናቸው።

ባለፉት አሥር ዓመታት በአማካይ ኢኮኖሚው በ4.7% ያደገ ቢሆንም (ሰንጠረዥ 2) በ3% እያደገ ካለው የህዝብ ቁጥር ጋር ሲመዛዘንና ካለንበት የድህነት አዘቅት ጋር ሲተያይ በሃገሪቱና በእያንዳንዱ ዜጋ ኑሮ ላይ ብዙም ለውጥ እንዳላመጣ መገንዘብ ይቻላል። በሰንጠረዥ 2 እንደተመለከተው የተለያዩ ሃገሮችን እድገት ብንመለከት (ሞዛምቢክ፡ ሱዳን፥ ዩጋንዳ፡ ወዘተ) ከዚህ የበለጠ እድገትም ማስመዝገብ ይቻል እንደነበር መገመት ይቻላል። ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶችን የኢኮኖሚ ባለሙያዎቹ የሚተነትኑት ሆኖ ከ1990 ዓ.ም. እስከ 2000 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ የብዙ ሃገራት ኢኮኖሚ እድገትም የመቀነስ አዝማሚያ አሳይቷል። በእርግጥ በዚህ ጊዜያት ውስጥ የሃገራችን ኢኮኖሚ በተቃራኒው እድገት ያሳየ ሲሆን በተለይም እስከ 1983 ዓ.ም. በነበረው የ1.1% አማካይ የኢኮኖሚ ዕድገት ልንገባበት እንችል የነበረውን የባሰና አስከፊ ሁኔታ በማጤን የ4.7% ዕድገት ተስፋ ሰጪ መሆኑን መመልከት ይቻላል። ግን በምንም መለኪያ በቂ ሊሆን አይችልም፣ አይደለምም፣ በዚህ ምክንያት አሁንም በድህነት ወስጥ የምንዳክር ሆነናል።

ሠንጠረዥ 2፡ አማካይ ዓመታዊ የGDP ዕድገት (%)

| ሀገር | 1980 - 90 | 1990 - 2000 |
|---|---|---|
| አልጄሪያ | 2.7 | 1.9 |
| አንጎላ | 3.4 | 1.3 |
| ባንግላዲሽ | 4.3 | 4.8 |
| ቤልጂየም | 2.1 | 2.0 |
| ቦትስዋና | 10.3 | 4.7 |
| ቻይና | 10.1 | 10.3 |
| ግብፅ | 5.4 | 4.6 |
| ህንድ | 5.8 | 6.0 |
| ኢራን | 1.7 | 3.5 |
| ኮሪያ | 8.9 | 5.7 |
| ማሌዥያ | 5.3 | 7.0 |
| ሞዛምቢክ | -0.1 | 6.4 |
| ናይጄሪያ | 1.6 | 2.4 |
| ሱዳን | 0.4 | 8.1 |
| ዩጋንዳ | 2.9 | 7.0 |
| ኢትዮጵያ | 1.1 | 4.7 |
| Sub Saharan Africa | 1.6 | 2.5 |

ምንጭ:- World Development Indicators Database, 2002

እስከዛሬ የሰራነው በቂ አይደለም፥ የሰራንበትም ፍጥነት ሳይለወጥ ከቀጠለ ከድህነት መቼውም የሚያወጣን አይሆንም የምንልባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ። በነበረንና አሁን በምንጓዝበት ፍጥነት ብቻ መጓዝ ከመረጥን መድረስ የሚገባን ቦታ ለመድረስ በርካታ አስርት ዓመታት የሚፈጅብን መሆኑን ማጤን ተገቢ ይሆናል። በተለይ ሁሉም ዜጋ የመንገድ፥ የውሃ፥ የቴሌፎን፥ የጤና የትምህርት ወዘተ አገልግሎቶች እንዲዳረሰው ለማድረግ በጣም ብዙ ዓመታትን ይጠይቀናል። 61% ላይ ያለውን የትምህርትና የጤና ሽፋን ለሁሉም ዜጋ በሚፈለገውና በሚገባው ጥራት ማዳረስ፥ በተደጋጋሚ እንዳየነው ድርቅ በመጣ ቁጥር እርዳታ ከመለመን መውጣት ወዘተ እስካሁን በመጣንበትና እየተጓዝንበት ባለው ፍጥነት ከሄድን መቼም የሚደረስበት እንደማይሆን ይህ ትውልድ ሊያየው የሚገባ ነው።

ከድህነት ወለል በታች ነን በምንልበት ጊዜ የመጨረሻዎቹ መሆናችንንም ማወቅ ያስፈልጋል። ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢያችን 100 ዶላር ብቻ ሲሆን ከዓለም ሀገሮችም የመጨረሻው ነው (ሠንጠረዥ 3)። ከፍተኛ የእዳ ጫና ካለባቸው ደሃ ሃገሮች (Heavily Indebted Poor Countries or HIPC) መካከል የነፍስ ወከፍ ገቢያቸው ከ200 ዶላር በታች የሆኑት ቻድ (200 ዶላር)፥ ጊኒ ቢሳው (180 ዶላር)፥ ማላዊ (170 ዶላር) እና ኒጀር (180 ዶላር) ብቻ ሲሆኑ የእኛ ከእነዚህም ሃገሮች በታች መሆኑንና ምን ያህል ዝቅተኛ እንደሆነ በአግባቡ መገንዘቡ የግድ ነው። ህዝባችን እያደገ ሲሄድ ኢኮኖሚው በተመጣጣኝ ባለማደጉ ምክንያት የነፍስ ወከፍ ገቢያችን እየቀነሰ መምጣቱም እጅግ አሳሳቢ ነው። ይህም ብዙ በጣም ብዙ ያለዕረፍት መስራት እንዳለብን የሚያመላክት ቀይ መብራት ነው።

## ሠንጠረዥ 3፡ ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ (በዶላር)

| ሀገር | ህዝብ ብዛት (ሚሊዮን)* | 1980 | 1995 | 1999 | 2000 |
|---|---|---|---|---|---|
| አልጄሪያ | 30.8 | 2,440 | 1,590 | 1.540 | 1.580 |
| አንጎላ | 13.5 | 800 | 340 | 410 | 430 |
| ባንግላዲሽ | 140.4 | 280 | 320 | 350 | 370 |
| ቤልጂየም | 10.3 | 18340 | 25,580 | 24.620 | 24.540 |
| ቦትስዋና | 1.6 | 2,730 | 3.520 | 3.490 | 3.650 |
| ካሜሩን | 15.2 | 960 | 660 | 600 | 580 |
| ቻድ | 8.1 | 280 | 210 | 210 | 200 |
| ቺሊ | 15.4 | 2,190 | 4,040 | 4.600 | 4.590 |
| ቻይና | 1284.9 | 320 | 520 | 780 | 840 |
| ኮንጎ | 52.5 | 230 | 150 | - | - |
| ግብፅ | 69.1 | 810 | 990 | 1.380 | 1.490 |
| ፈረንሳይ | 59.4 | 19,660 | 24,700 | 24.290 | 23.810 |
| ጀርመን | 82.0 | 20,290 | 27,920 | 25.680 | 25.120 |
| ኢንዶኔዥያ | 214.8 | 620 | 1,000 | 580 | 570 |
| ኬንያ | 31.3 | 380 | 260 | 360 | 350 |
| ደቡብ ኮሪያ | 47.1 | 5,740 | 10,250 | 8.480 | 8.960 |
| ማሌዥያ | 22.6 | 2,380 | 4,030 | 3.370 | 3.370 |
| ሞዛምቢክ | 18.6 | 170 | 140 | 220 | 230 |
| ናይጄሪያ | 116.9 | 270 | 210 | 250 | 260 |
| ሱዳን | 31.8 | 600 | 290 | 320 | 350 |
| ስፔን | 39.9 | 11,790 | 14,360 | 14.920 | 15.080 |
| ቱርክ | 67.6 | 2,270 | 2,800 | 2.880 | 3.080 |
| ደቡብ አፍሪካ | 43.8 | 2,890 | 3,740 | 3.190 | 3.060 |
| ኢትዮጵያ | 64.5 | 160 | 110 | 100 | 100 |
| Sub Saharan Africa | 633.8 | 550 | 520 | 500 | 480 |
| Low & middle income | | 890 | 1,050 | 1.130 | 1.160 |

ምንጭ:- World Development Indicators Database, 2002;
**The State of the World's Children 2003*, UNICEF, 2002.

የዓለም መሪዎች በ2000 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ባደረጉት ስብሰባ የቀረፁት ሚሊኒየም ዴቨሎፕመንት ጎል ዋነኛ መፈክር *We will spare no effort to free our fellow men, women, and children from the abject and dehumanizing conditions of extreme poverty, to which more than a billion of them are currently subjected* ይላል፡፡ በዚህም መሰረት የተባበሩት መንግሥታት ሚሊኒየም ዴቨሎፕመንት ጎል በ2015 ዓ.ም. በሁሉም ህዝቦች በ1990 ዓ.ም. የነበራቸው የድህነት መጠን በዓለም በግማሽ መቀነስ አለበት፥ ለዚህም ሀገራት በዓመት ከ7 - 10% የማያቋርጥ የGDP ዕድገት ሊኖራቸው ይገባል ብሎ ያስቀምጣል፡፡ ይህም በእኛ ሁኔታ

የ3% የህዝብ ዕድገት ያለ በመሆኑ የኢኮኖሚ ዕድገታችን ሳያቋርጥ ከ10% በታች ሳይወርድ ማደግ አለበት ማለት ሊሆን ይችላል።

በተመሳሳይ ከድህነት ወለል በላይ ለመምጣት የዓለም ባንክ እንዳስቀመጠው የእያንዳንዱ ዜጋ የቀን የነፍስ ወከፍ ገቢ ከአንድ ዶላር ማነስ እንደሌለበት ያመለክታል። በዚህም እሳቤ እኛ አሁን ያለንን ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ 365 ዶላር ማድረስ ይጠበቅብናል ማለት ሊሆን ነው። ይህ ደግሞ እስካሁን በሄድንበት ፍጥነት ሊደረስበት የሚችል አይሆንም። በእርግጥ ባልፈጠነው አካሄዳችን በአማካይ 4.7% የኢኮኖሚ ዕድገት ካስመዘገብን 10% የማያቋርጥ ዕድገት ለማምጣት ቁርጠኝነቱና ዝግጅቱ ከተያዘ የማይቻል አይሆንም ።

በዚሁ ድህነታችን ከቀጠልንና በተለይም ከህዝብ ብዛት ጋር የሚመጣውን የባሰ ድህነት ከመረጥን አደጋው የእያንዳንዱ ዜጋ የህልውና ጥያቄ ወደመሆን ይደርሳል። ይህም ተስፋ መቁረጥን፥ መኖር አለመቻልንና ጥፋትን ሊያስከትል እንደሚችል ከወዲሁ መገመት ይገባናል፥ መረዳትም አያዳግትም።

**ሠንጠረዥ 4፡ የGDP ዕድገት በተለያዩ ሃገራት** (በቢሊዮን ዶላር)

| ሀገር | 1980 GDP | 1998 GDP |
|---|---|---|
| ቻይና | 201,687 | 960,924 |
| ቺሊ | 27,572 | 78,025 |
| ግብፅ | 22,912 | 78,097 |
| ኬንያ | 7,265 | 11,083 |
| ማሌዥያ | 24,488 | 71,302 |
| ደቡብ ኮርያ | 63,803 | 297,900 |
| ስፔን | 213,308 | 551,923 |
| ዩጋንዳ | 1,244 | 6,653 |
| ኢትዮጵያ | 5,179 | 6,568 |

ምንጭ፡- World Development Report, 2000

እስካሁን ከተጓዝንበት ፍጥነት በላይ መጓዝ በጣም አስቸጋሪና እንዲያውም አይቻልም የሚሉ ወገኖች እንደሚኖሩ ይገመታል። በዓለም ዙሪያ በተለያዩ ሃገራት እንደታየው በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ለውጥና ዕድገት ማምጣት እንደሚቻል ተዘግቧል፥ በግልጽም እማኝ የሚሆኑ ሃገራት አሉ (ሰንጠረዥ 4)። እ.ኤ.አ. ከ1980 ዓ.ም. እስከ 1990 ዓ.ም. ባሉት ዓመታት የሃገራችን GDP ያደገው ከ25% ብዙም ባልበለጠ መጠን ብቻ ነው። በቻይና ግብፅ ማሌዥያ ደቡብ ኮርያና ዩጋንዳ በእነዚህ 18 ዓመታት ወስጥ የየሃገራቱ

GDP በ3 እና ከዚያ በላይ እንደገና በሌሎቹ (ቺሊ, ኬንያና ስፔን) ደግሞ ሁለት እጥፍና ከዚያ በላይ እንዳደገ ይታያል። ስለዚህ የኢኮኖሚ ዕድገት በሁለት፥ ሶስትና ከዚያ በላይ እጥፍ በሆነ ደረጃ ማሳደግ የማይቻልበት ምንም ምክንያት የለም። የሚፈለገውንና የሚገባውን ያህል አይሁን እንጂ በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ የዕድገት ተግባራትን መስራት እንደሚቻልም የሃገራችን ያለፉት አሥር ዓመታት አሳይተውናል። ከላይ የቀረቡት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት እጅግ ፈጥነን ለመንቀሳቀስና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታውንና ልማቱን የማፋጠን ዓላማ ይዘን ለመጓዝ ቁርጠኝነትና ቁጭት ከያዝን ፈጣን ዕድገት ለማምጣት የማንችልበት ምንም ምክንያት የለም።

## የከፍተኛ ትምህርት ሁኔታ

የሃገራችን የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ እጅግ ወደኋላ የቀረ ነው (ሠንጠረዥ 5 እና 6)፥ ከብዙ ሃገራት ተሳትፎ ምጣኔም በጣም ያነሰ ነው። ምጣኔው ብቻ ሳይሆን ከህዝቡ ብዛት እድገት ጋር ተነፃፅሮ ሲታይ ደግሞ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆናችንን በጉልህ ያሳየናል። የተሳትፎ ምጣኔው ከሰሃራ በታች ላሉ ሃገሮች ከተቀመጠው አማካይ በጣም ያነሰ ነው (ሰንጠረዥ 5)። በኢትዮጵያ ዕድሜው ለዚህ የትምህርት ደረጃ ከደረሰው ዜጋ ተሳታፊ የሆነው ከ1% ብዙም ያልበለጠ ሲሆን የሰሃራ በታች አገሮች አማካይ ከ3% ያላነሰ ነው።

ሠንጠረዥ 5፡ የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ

| | የተማሪዎች ብዛት | | የተሳትፎ ምጣኔ (%) | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሃገር | 1985 | 1995 | 1985 | 1995 | 1998 |
| አፍጋኒስታን | 22,306 | 26,360 | 2 | 2 | - |
| አልጄሪያ | 132,057 | 347,410 | 9 | 12 | 14.9* |
| ቤልጂየም | 247,498 | 352,630 | 31 | 56 | 56.9* |
| ቦትስዋና | 1,938 | 7,920 | 2 | 5 | 5.8 |
| ካሜሩን | 21,438 | 47,665 | 2 | 4 | 5.2* |
| ኮንጎ | 40,878 | 93,266 | 2 | 2 | 2.3 |
| ግብፅ | 854,584 | 850,051 | 20 | 20 | 20.2 |
| ኢራን | 239,300 | 1,048,093 | 5 | 17 | 17.6 |
| ኬንያ | 21,756 | 67,371 | 1 | 2 | 2 |
| ደቡብ ኮሪያ | 1,455,759 | 2,225,092 | 34 | 52 | 87.7 |
| ሱዳን | 37,367 | 82,901 | 2 | 4 | 6.8* |
| ቱርክ | 469,992 | 1,174,299 | 10 | 18 | 21 |
| ዚምባብዌ | 30,843 | 45,593 | 3 | 6 | 6.6 |
| ኢትዮጵያ | 27,338 | 35,027 | 1 | 1 | 1.3* |
| Sub Saharan Africa | - | - | 2 | 3 | - |
| OECD | - | - | 37 | 58 | - |

ምንጭ፡- HEd. In Developing Countries: Peril & Promise, 2000; *Unesco Institute for Statistics, 2002.

በኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት አጠናቆ የሚወጣውን ምሩቅ በተመለከተም በዲፕሎማና ዲግሪ ደረጃ የሚሰለጥነው የሰው ኃይል ከ100 ሺህ ህዝብ ውስጥ ከ60 ብዙም ያልበለጠ ነው (ሠንጠረዥ 6)። ይህ ማለት ወደ ስራው ዓለም የሚሰማራና ስራ ፈጣሪ የሆነ በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሃይል እጥረት አለ ማለት ነው። ባለፉት ጥቂት ዓመታት መሻሻል የታየ ቢሆንም ምጣኔውንም ሆነ የተመራቂውን ብዛት ብዙም ያሳደገው አይደለም። በዚህ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሃይል እጥረት ደግሞ የኢኮኖሚውን እድገት፡ ኢንቨስትመንቱን፥ የማህበራዊ አገልግሎቶችንና የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን ሂደትና ፍጥነት ይጎትተዋል፥ ይጎዳዋል።

ሠንጠረዥ 6፡ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪ ብዛት ለ100 ሺ.ህ ህዝብ

| ሃገር | 1980 | 1985 | 1995 |
|---|---|---|---|
| አልጄሪያ | 530 | 798 | 1,236 |
| ቤልጂየም | 2,111 | 2,511 | 3,494 |
| ቦትስዋና | 120 | 180 | 546 |
| ካናዳ | 4,035 | 6,320 | 6,984 |
| ኮንጎ | 105 | 129 | 212 |
| ግብፅ | 1,751 | 1,717 | 1,900 |
| ህንድ | 515 | 582 | 613 |
| ኢራን | 317 | 469 | 1,533 |
| ደቡብ ኮሪያ | 1,698 | 3,568 | 4,974 |
| ሱዳን | 154 | - | 245 |
| ቱርክ | 554 | 934 | 1,960 |
| ዚምባብዌ | 117 | 368 | 626 |
| ኢትዮጵያ | 37 | 66 | 62 |
| Sub Saharan Africa | 117 | 124 | 339 |
| OECD | 3,033 | 3,197 | 4,071 |

ምንጭ፡- HEd. in Developing Countries: Peril & Promise, 2000

## ፈጣን ልማትና የዲሞክራሲ ባህል ግንባታ እንዴት ይመጣል?

ታዳጊ በሆኑትም ሆነ ባደጉት ሃገራት ፈጣን ልማትና ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል በዚህ ፅሁፍ የመጀመሪያ ክፍል የቀረቡት ማብራሪያዎችና ሰንጠረዦች ያመለክታሉ። ስለዚህ ቁርጠኝነቱና ቁጭቱ ካለ በአጭር ጊዜ ውስጥ ዕድገትና ለውጥ ማምጣት ይቻላል። እኛ ታዲያ በተመሳሳይ ለማደግ፡ ለመለወጥና ለመበልፀግ ለምን አልቻልንም? የማይቻል በመሆኑ እንዳልሆነ የብዙ ሃገራት ተመክሮ እንደሚቻል አሳይቶናል። ያለብን

መሰረታዊ ችግር ምንድነው ብሎ መመርመርና የመፍትሄ አቅጣጫዎች ማስቀመጥ የግድ ይሆናል፡፡

በመጀመሪያና በዋነኛነት የድህነታችንን አስከፊነት እያንዳንዱ ዜጋ በአግባቡ ተገንዝቦና የሚያመጣውንም አደጋ አጢኖ ያለመንቀሳቀስ ችግር አለብን፡፡ ከዚህ ድህነትም ለመውጣት እንደሚቻልና በተለይም ይህ የተማረው ትውልድ ማንኛውንም መስዋዕትነት ከፍሎ እራሱን ከድህነትና ችግር ለማውጣትና ይህንንም ሲያደርግ አብሮ በድህነት ያስተማረውን ህዝብ ከችግር ለማውጣት ኃላፊነትና ግዴታ እንዳለበት አውቆ በስፋት ጥረት ማድረግ አይስተዋልም፡፡

ሃገራዊ የሆነ ትክክለኛና ከድህነት የመውጣት መሪ አስተሳሰብና አመለካከት አለን ብለን እናምናለን፡፡ ይህም በህገ መንግስቱ በወጡ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በግልጽና በዝርዝር ተቀምጧል፡፡ እነዚህም አመለካከቶች በመኖራቸው ነው በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ባለፉት አሥር ዓመታት የተመዘገቡ ውጤቶች ሊመዘገቡ የቻሉት፡፡ እነዚህ መሪ አመለካከቶች ትክክለኛ ሆነው የተቀረፁ ቢሆንም በሚፈለገውና በሚገባው ደረጃ ሁሉም ተገንዝቦአቸዋል፥ ተግባራዊም ለማድረግ በጋራ ራዕይ እየተንቀሳቀሰ ነው ለማለት አያስደፍርም፥ አይደለም፡፡

መሪዎች፥ ምሁራን፥ ሲቪል ሰርቪሱ በአጠቃላይም ህብረተሰቡ ዘንድ ይህ ትክክለኛና መሪ አመለካከት በአግባቡ አልደረሰም የሚባልበት ዋነኛ ምክንያት የሚፈለገውና የሚገባው ውጤት በፍጥነት ባለመገኘቱ ምክንያት ነው፡፡ በአግባቡ ወደ እያንዳንዳችን የደረሰ ቢሆን ህዝቡ አውቆታል፡ አምኖበት ተቀብሎታል፥ ካመነበት ደግሞ ይጠቅመኛል፡ ለውጥ ያመጣልኛል ብሎ ይይዘዋል ማለት ነው፡፡ በዚህ መልኩ ከያዘው ለተግባራዊነቱ ይንቀሳቀሳል፥ ሲተገብረው ደግሞ የሚያደናቅፈውን አመለካከት ወይም አሰራርም የሚታገልና የሚፃረርም ይሆናል፡፡ የሚያደናቅፈውን ሁሉ ለመወጣት ሲታገልም በተነሳሽነትና ፈጠራን ጨምሮበት ይሆናል፡፡ የእዚህ ዓይነት አመለካከት በእያንዳንዳችን ሰርጿል፡ ተግባራዊም ለማድረግ እየተንቀሳቀስን ነው ማለት አይቻልም፡፡

ይህ መሪና ትክክለኛ አመለካከት ወደ እያንዳንዳችን እንዳይደርስ፡ እንዳይሰርፅ አስተዋፅዖ ያበረከቱ በርካታ ምክንያቶች ማቅረብ ይቻላል፡፡ በዋነኛነት ሊጠቀስ የሚችለው ግን እያንዳንዳችን ከድህነት ለመውጣት፡ ሃገራችንና ህዝቡንም አብሮ ለማውጣት፥ እንዲሁም ከፀረ-ዲሞክራሲያዊ ባህልና አሰራር ለመላቀቅ ቁርጠኝነት አለማሳየታችን ነው፡፡ ከዚህ ቁርጠኝነት ይልቅ ባለው የመቀጠል፥ ችግር የለብንም የማለትና

በአጠቃላይም በትንሽ ስኬት የሚረካ (complacent) የመሆን አዝማሚያ፡ አስተሳሰብ አለብን። አመራሩ፥ ሰራተኛውና በተለይም ትልቁ ኃላፊነት ያለበት ምሁሩ ከውርደት እንውጣ የሚል እልህ በብቃት አይታይበትም፡ ህዝቡም በእልህና በቁጭት ከድህነት ለመውጣት እንዲነሳሳ በብቃት አያስተላልፍም። በአጠቃላይ እያንዳንዱ ዜጋ ደሃ መሆኑ፡ ራሱን መመገብ ያልቻለ መሆኑ፥ ዲሞክራሲያዊ ባህል ባልተገነባበት ባህር ውስጥ ያለ መሆኑ የሚያሳፍረው፥ ተዋረድኩ የሚልበትና የሚቆጭበት ወቅት ላይ ነን።

ድህነታችን እየባሰ ሲሄድና ህዘቡ እየተራበ ሲመጣ ሃብት የሚያመነጭና የሚያፈራው ሰፊው ህዝብ ችግር ላይ ነው ማለት ነው። ይህ የገጠሩ ህዝብ ወደባሰ ችግርና ድህነት ወደቀ ማለት ደግሞ ሲቪል ሰርቪሱና ምሁሩ ገቢው እንዲጨምርና ኑሮው እንዲሻሻል የሚያበቃው ሁኔታ አልተመቻቸም፡ አልጎለበተም ማለት ነው። ስለዚህ አሁን ካለንበት የድህነት አዘቅት ለመውጣት በጋራ ከመነሳት፥ መስዋዕትነት ለመክፈል ከመድከም ይልቅ ያላፈራነውን የማይገባንን ሃብት በተጨማሪ እንዲሰጠን መጠየቁ ተገቢ አይሆንም። በውርደታችን፥ በድህነታችንና ሃብት አመንጪው እየተራበ እኛ ከመቆጨትና ለመለወጥ ከመሯሯጥ "ለእኔ የበለጠ ይገባኛል" እያልን ያለብንን ኃላፊነት ችላ እንላለን።

ፈጥኖ ለመጓዝ፥ የስራ ባህላችንን ለማጎልበት፥ በጋራ በማደግ ብቻ የእያንዳንዱ ህይወትና ኑሮ እንደሚሻሻል ታሳቢ ለማድረግ፥ ወዘተ የአመለካከት ለውጥ ማምጣት የግድ ቢሆንም ይህ ለውጥ ብዙ ጊዜ ይፈልጋል እያልን ላለመንቀሳቀስ ምክንያት እንሰጣለን። የወደፊቱ ትውልድ ላይ የምናቆየውን አደጋ አሻግረን ማየት አንፈልግም። በአራት አምስት እጥፍ ብቻ ሳይሆን በአስርና ከዚያ በላይ እጥፍ እድገት ማምጣት እንችላለን የሚል ግንዛቤና ቁርጠኝነት አልያዝንም፥ አናስተላልፍም። ባብዛኛው ዛሬ 'ለእኔ' የተሻለ ሁኔታ ካልተፈጠረ ወደፊት መሄድ አንችልም እንላለን ወይም በለየለት መልኩ ከሃገር በመልቀቅ ያላስተማረን፡ ያልተቸገረብንና ወጪም ያላወጣብን ህብረተሰብን ሙያ፡ ችሎታችንና ስብዕናችንም ዝቅ አድርገን ለማገልገል እንመርጣለን። በእርግጥ ባደጉት ሃገራት የተሻለ ገቢና የተመቻቸ የሥራ ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል አያጠያይቅም። ውርደቱ ግን እዚያም ሄደን እንደማይለቀን በአግባቡ ተገንዝበነዋል ለማለት አያስደፍርም።

ፈጣን ልማት ሊመጣና ዲሞክራሲያዊ ባህልና ሥርዓት ሊገነባ የሚችለው ቀደም ሲል እንደተገለጸው ትክክለኛና መሪ ሃሣብ ሲኖርና ይህም አመለካከት ወደ ህዘቡ፥ እና ወደ እያንዳንዱ ዜጋ ደርሶ ሲፀርፅ፥ እምቅ ኃይል ብሎም በዋነኛነት እምቅ ቁሳዊ ሃይል (material force/ potential)

ሲሆንና ብሄራዊ መግባባትን ፈጥሮ የጋራ ራዕይ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ብሔራዊ መግባባት ተፈጠረ፥ የጋራ ራዕይ ተያዘ የምንለው ደግሞ በመተማመን ሁሉም ዜጋ የተቀበለውና የራሱ ዕምነትና አመለካከት ካደረገው ሲሆን እንዲሁም ለህብረተሰቡ የሚጠቅም በመሆኑና ውጤትም እንደሚያመጣ ሲታመንበት ብቻ ነው፡፡

ውጤት የሚያመጣ መሪ አስተሳሰብ በህብረተሰቡ እይታ ቁልፍ የሆኑና አበይት ተብለው የሚፈረጁ ተግባራት ይኖረዋል፡፡ ከመሰረታዊ ችግሮች የሚመነጩ ቁልፍ ተግባራትና አበይት ተግባራት ቅደም ተከተል ወጥቶላቸውና ትክክለኛ የአፈፃፀም አቅጣጫ ተቀምጦላቸው ተግባራዊ ሲደረጉ ውጤት ያመጣሉ፥ ልማትን ያፋጥናሉ፥ ከድህነት መውጫ መንገድ ይሆናሉ፡፡ ከቁልፍ ተግባር ቀጥለው የሚቀመጡት አበይት ተግባራት ደረጃቸውና የሚያሳድሩት ተፅዕኖ ተለይቶ በቅደም ተከተል እንዲቀመጥና የእያንዳንዱም ገፅታ ምን እንደሆነ ማመልከት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ቅደም ተከተል የሰው ኃይል፥ የገንዘብ፥ የጊዜ፥ ወዘተ ሃብት አመዳደብን የሚወስን ይሆናል፡፡ ቁልፍ ተግባራቱን ለመለየት የሁኔታዎች/የአካባቢ ብቁ ዝርዝር ግምገማ ማካሄድና የተለዩትን ትንታኔዎችና ችግሮች እንደየባህርያቸው በየፈርጁ ማድረግን ይጠይቃል፡፡ የቁልፉ ተግባር መከናወን የቁልፍ ችግር መፈታት የሚያመቻችና የሚያመጣ ይሆናል፡፡ በሃገር አቀፍ ደረጃ ዋናው ቁልፍ ተግባር የአቅም ግንባታ ስራ መሆኑ በዚህም ውስጥ ትምህርትና ስልጠና የመጀመሪያውን ረድፍ የሚይዝ እንደሆነ በመንግስት የፖሊሲና ስትራቴጂ ሰነዶች በግልፅ ተቀምጧል፡፡

ባለፈው መስከረም ተቋማት በጋራ በነደፉት መርሃ ግብር ዋነኛው ቁልፍ ተግባር የከፍተኛ ትምህርት የአመራር ስርዓትን ፈትሾ ማሻሻያዎችን ባፋጣኝ መውሰድ እንደሆነ ተቀምጧል፡፡ ይህ ቁልፍ ተግባር ሲከናወን ብዙዎቹ የዘርፉ ችግሮች እንደሚፈቱ እምነት አለ፡፡ በዚህ ረገድ ምን አከናወንን? ቀጣይነት ያለውንና በውጤቱም ከድህነት የመውጣትና የዲሞክራሲ ባህል የመገንባት ትክክለኛ መንገድ ውስጥ እንደሚያስገባን አምነንበት እየተንቀሳቀስን ነው? እየፈጠንን ነው? ወይንስ የአንድ ጊዜ ስራ አድርገነው ተጠናቅቋል ብለን ቆመናል? የሚሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ማንሳትና በየጊዜው ምላሽ መስጠት ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡

የየተግባራቱ ማከናወኛ የአፈፃፀም አቅጣጫውም በትክክል ስለሚቀመጥና የጋራ ራዕይ ስለሚያዝበት ብሔራዊ መግባባት የሚፈጥር እንዲሁም የሚፈለገውንና የሚገባውን ፈጣን ለውጥ በሚፈለገው ጊዜ ለመፈጸምና ይህም ለውጥ ጥራት ያለው የማኅበረሰብን ለውጥ (transformation)

የሚያመጣ ይሆናል። ይህ የአፈፃፀም አቅጣጫ ቁልፍና አበይት ተግባራትን በእንቅስቃሴ (movement) መልክ የሚያከናውን የፈጻሚዎችን ተጨባጭና ትርጉም ያለው ተሳትፎ (real and meaningful participation) ያረጋገጠና፡ ፈጻሚዎች ከአፈፃፀማቸው ከልምዳቸው እየተማሩ የሚሄዱ ያደረገ ሲሆን ብሔራዊ መግባባቱን ያጠናክረዋል፥ ፈጣን ልማትና የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ እንዲመጣ ያስችላል።

በዚህ ረገድ የብዙሃን ንቅናቄን ለማምጣት መሪ ሃሳቦች ከአመራሩ ቢመነጩም ብዙሃኑን ፈጻሚ ያሳተፉና መግባባትም የተደረሰባቸው ማድረግ ተገቢ ነው። የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሃላፊዎች በጋራ የነደፏቸው መርሃ ግብሮች ምንነት፥ ከእነዚህ ቁልፉ ተግባር ምን እንደሆነና የዚህ መከናወን ፋይዳ፥ የዝርዝር ተግባራቱ፥ ውጤት ወዘተ ጉዳዮች ላይ የተቋማቱን ማህበረሰብ ለማሳወቅ ለማሳመን፥ እንዲቀበለውና አምኖበት በባለቤትነት ይዞት ለተግባራዊነቱና ስኬቱ እንዲንቀሳቀስ ያደረግነው ጥረት ምን ያህል ነው? በዚህስ ረገድ ምን ያህል ተሳክቶልናል? በብዙዎቹ ተቋማት ጥረቱም ሆነ ስኬቱ ከፍተኛ የነበረ ሲሆን፥ በቀጣይነቱ ላይ ግን ልዩ ትኩረትን የሚሻ እንደሆነ ይገመታል።

ህብረተሰቡን ማንቀሳቀስ አለመቻል ስራዎቻችን በአግባቡና በወቅቱ እንዳይከናወኑ የተለያዩ የጥገኝነት አስተሳሰቦች እንዲሰፍኑ፡ ብሎም መድረስ የምንፈልግበትና የሚገባን የእድገት ደረጃ ላይ በጋራ እንዳንደርስ አሉታዊ አስተዋፅዖ (negative impact) እንደሚኖረው መገመት አያዳግትም። የጥገኝነት አስተሳሰቦች የምንላቸውን በተለያዩ መንገዶች መግለፅ ይቻላል። ለምሳሌ ደመወዛችንና አበላችን እስከዚህ ቀን ድረስ ካልተስተካከለ ስራ እናቆማለን በማለት ለተማሪው/ስልጣኙ፥ ለታካሚዎችና ለህብረተሰቡ ግድየለሽ መሆን ወይም በብዙ ሚሊዮን ብር ወጪ ለመማር ማስተማሩ ድጋፍ መሳሪያዎች ተገዝተው ተቋም ደርሰው ተረክቦ በእራስ ባለሙያም ቢሆን አስተክሎ ስራ ላይ ለማዋል ባለቤት ለመሆን በተቆርቋሪነት ስሜት የሚደረግ እንቅስቃሴ በአንዳንድ ተቋማት ሃላፊዎችና መምህራን አለመታየቱ፥ ወይም ፈጥነን ላለመጓዝ ደንቦችን መመሪያዎች ይጎትቱናል የማለት እንጂ እነዚህ እንዴት መሻሻል እንደሚገባቸውና ልንወጣቸው እንደሚገባ በቁርጠኝነት አለመታገል፥ ወይም በጽናት ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት የሚሰራውንና ውጤት ያለው ተግባር ያከናወኑ ግለሰቦችን ወይም ተቋማትን እውቅና (recognition and reward) አለመስጠት በተጓዳኝም የማይሰራውን በቁርጠኝነት አለማብቃት ወይም አለማስወገድ ወዘተ. የጥገኝነት አስተሳሰቦች ሆነው በተቋማት የሚታዩ ናቸው።

መሪው አመለካከትና አስተሳሰብ በህብረተሰቡ ውስጥ የቆየውንና ለዕድገትና ለልማት ፋይዳው ውስን የሆነውን እምነት (conviction) በማስወገድ አዲስ ለውጥና መሻሻልን እንደሚያመጣ፥ ለህዝቡ ጠቀሜታው የጎላ እንደሆነ፡ ጠቀሜታው እንዴትና መቼ እንደሚጠቅመው በግልጽ በማስቀመጥ ማሳመን እና ማንቀሳቀስ ያስፈልጋል። በተቀረጸው አመለካከት ላይ መተማመንና መግባባት ከተያዘ በብዙሃኑ ፈጻሚ አካል ተሳትፎ ትክክለኛ ዕቅድ ማዘጋጀት፥ በአፈፃፀሙ ፈጻሚው ዕምነት (confidence) እንዲኖረው፡ የእራሱ ዕውቀት እንዲያደርገውና ለተግባራዊነቱም ቁርጠኝነት (commitment) እንዲያመጣ ማስቻል ይጠበቃል፥ ይቻላል።

አመራሩ በምንም ዓይነት ብዙሃኑን ተክቶ ፈጻሚ ሊሆን አይችልም፡ አይገባውምም። ስለዚህ ይህንን ንቅናቄ በቅርብ መምራት፥ መከታተልና መደገፍ የሚችል ብቁ አመራር ማስቀመጥ ተገቢ ይሆናል። አመራሩ የዲሞክራሲ ባህል ያለው፥ ንቅናቄው ዳር እስኪደርስ የሚያጋጥሙ መሰናክሎችን (challenges) እንዴት ሊፈታ እንዳሰበና እንደተንቀሳቀሰ በመከታተል የሚያበረታታና የመፍትሄ አቅጣጫ የሚያመላክት መሆን አለበት። ስራንና ውጤትን ማዕከል ያደረገ ተከታታይ ግምገማ በማካሄድ ከመነሻው የነበሩ ጥርጣሬዎችን በማስወገድ፥ ካልተሳኩ ጥረቶች በመማርና በራስ መተማመንን በማጎልበት የንቅናቄው ሂደት የማይናወጥ መሰረትና ድምዳሜ እንዲኖረው ማስቻል የግድ ይሆናል።

ትክክለኛና መሪ አመለካከትን በጋራ በመያዝ፥ ቁልፍ ተግባራቱን በአግባቡ ለይቶ በመንቀሳቀስና ህብረተሰቡን በንቅናቄ መልክ በማሳተፍ የልማትና የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታውና ከድህነት የመውጣቱ የፍጥነት አካሄድ የተደቀነብንን አደጋ በቀደመ መልኩ እንዲከናወን የሚያስችል አቅም ይፈጥራል፥ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። አጠቃላይ አካሄዱ የአመለካከትና የአሰራር ለውጥና ዝርዝር ስራን በጥልቀት መስራትንና በቁጭት መንቀሳቀሱን የሚጠይቅ ነው። አድካሚ ስራ ቢሆንም መስራት የሚቻል ነው፥ የሚገባም ነው። በዚህ ረገድ በየደረጃው ያሉ መሪዎች አምነውበት፡ በማሳመን ንቅናቄውን የመምራትና ዳር የማድረስ ጥረትና ከፍተኛ ኃላፊነት አለብን።

## በሀገር ልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ሚና

በሀገራዊ የአቅም ግንባታ ስትራቴጂ ውስጥ ከፍተኛ ትምህርት ቁልፍ ሚና አለው። ትምህርት የዕድገት ቁልፍና ወሳኝ መሰረት ነው። በስንጠረዥ 7

እንደተመለከተው የተለያዩ ሃገሮች የኢኮኖሚ እድገት ያሳዩበት አንዱ ምክንያት ዜጎች የበለጠ ጊዜ በትምህርት ላይ ማሳለፋቸውና ትምህርትና ስልጠና ማግኘታቸው ነው። የትምህርት ቤት ቆይታ በሚባልበት ጊዜ የትምህርት ደረጃቸው እየተሻሻለና እያደገ መሄዱን የሚያመላክተን ነው። በእነዚህ ሃገራት የትምህርትና ስልጠና መስፋፋት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ለውጥና እድገት እንዳመጣ መገንዘብና ከዚህም ተመክሮ መውሰድ ያስፈልጋል።

ሠንጠረዥ 7፡ በትምህርት የሚታይ የኢኮኖሚ እድገት

| ሃገር | ዓ.ም. | የ15-64 ዓመት ዜጎች የትምህርት ቤት ቆይታ ጊዜ (ዓመት) | ግድፕ (ጥስድ) |
|---|---|---|---|
| ቺሊ | 1960 | 6.19 | 4000 |
| | 2000 | 10.00 | 7000 |
| ማሌዥያ | 1960 | 3.22 | 2000 |
| | 2000 | 9.31 | 6000 |
| ታይላንድ | 1960 | 2.60 | 1500 |
| | 2000 | 7.51 | 4000 |

ምንጭ፡ Unesco/OECD Study, Financing Education, 2000

የሃገራችን የማስፈጸም አቅም ግንባታ የሰው ሃይልን በብዛትና በጥራት የማፍራት፥ አሰራሮችን የማሻሻልና ተቋማዊ ሁኔታዎችን ማጎልበትና ማቋቋምን ማዕከል አድርጎ የሚከናወን ስትራቴጂ ነው። እነዚህን መሰረታዊ ጉዳዮችም በብቃት ለማሳካትና ለመለወጥ ከፍተኛ ትምህርት ትልቅ ኃላፊነት አለው።

የከፍተኛ ትምህርት፡-

- ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትንና ባህልን የመገንባት፥
- በዕውቀት፥ በክህሎትና በአስተሳሰብ ብቁ የሆኑ ዜጎችን የማፍራት፥
- ሀገራዊና ማኅበራዊ ችግሮችን ፈቺ የሆኑ ብቁ ምርምሮችን የማካሄድና
- ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ የአሰራር ሥርዓቶችን ተግባራዊ የማድረግና በዚሁ መርህ የመንቀሳቀስ ዋነኛ ዓላማዎች እንደሚኖሩት በተለይ ከቅርብ ጊዜ በፊት በተደረጉ ውይይቶች መግባባትና ስምምነት የተደረሰባቸው ናቸው።

እነዚህን ዋነኛ ዓላማዎች ለማሣካት እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ ምን ይመስላል? ዓላማዎቹ የትኩረት አቅጣጫ ለውጦችና ተቋማት የሚጠበቅባቸውን በአግባቡ የመወጣት ኃላፊነት በእያንዳንዱ ተቋም፡ ኃላፊና ግለሰብ በተገቢው ግንዛቤ ተይዞበታል? ሠርጿል? የዕለት ተዕለት ተግባራችንስ ይህንን የተከተለ ነው? የሚፈለገው ውጤትስ በጣም በፈጠነ መልኩ መድረስ ያለበት መሆኑን ታሳቢ እያደረግን ነው የምንጓዘው? የሚሉትን ጥያቄዎች በየቀኑ፥ በየቦታው፥ በእያንዳንዱ የሥራችን ሂደት ልንጠይቃቸውና በትኩረት ልናጤናቸው የሚገቡ ናቸው። የዓላማዎቻችን በፍጥነት መሣካት ለሃገር ልማትና ዕድገት ብሎም ከድህነት ለመውጣት ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። የዓላማዎቹ አለመሣካት ወይም በዝግመት መሣካት ደግሞ በአስከፊ ድህነት ውስጥ የመቆየትን፡ የህዝባችን የኑሮ ሁኔታ ማረጋገጥ ማለት ነው።

የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ መጠንም ሆነ የተማሪው ቁጥር በጣም ዝቅተኛና ከብዙ ሃገራትም በታች በመሆኑ፥ የሃገራችን ድህነትና የነፍስ ወከፍ ገቢያችን ከዓለም መጨረሻ ላይ ያስቀመጠን በመሆኑ የልማትና የለውጥ ዋነኛ መሣሪያ በሆነው ትምህርት ዘርፍ ምን መሥራት ይጠበቅብናል? መቼ? እንዴት? ብሎ መጠየቅ ወቅታዊ ነው። በየተቋሙ የምንጠቀምበት ስርዓተ ትምህርት ስልጣኙ ስራ ፈጣሪ፡ ሃላፊነት የሚሰማውና መሸከም የሚችል፥ የሃገሩን ሁኔታ በአግባቡ የተረዳና ከስልጠና በኋላም የእራሱንና የህብረተሰቡን ኑሮ ለመለወጥና ችግር ለመፍታት የሚጥርና አስተዋፅዖ የሚያደርግ ወይም የሚያበቃ መሆን መቻል አለበት። በየዘርፉችን የምናደርጋቸው ምርምሮች የተቀናጁ፡ በሃገር ችግር ላይ ያተኮሩ፥ መፍትሄ የሚያመነጩና ከድህነት ለመውጣት የሚያስችሉ መሆን ይገባቸዋል። በመማር ማስተማሩም ሆነ በምርምር ዘርፎች ችግሮቻችንን በሙሉ መለየትና በቅደም ተከተል በማስቀመጥ መፍትሄዎችንም በአፋጣኝ መተለም ይጠበቃል።

እስካሁን እየተደረጉ ባሉ የለውጥ ሂደቶች እንዲሁም የማስፋፋትና የማጠናከር ስራዎች የአብዛኞዎቹ ተቋማት መሪዎችና ማህበረሰብ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ ለመንቀሳቀስና በባለቤትነት ይዞ ለመጓዝ የሚደረግ ጥረት፡ እንዲሁም የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት የሚከናወኑ ተግባራት አበረታች ናቸው። ይሁን እንጂ በሚፈለገውና በሚገባው መጠንና ጥራት ነው ማለት ግን አያስደፍርም በተወሰኑ አካባቢዎች/ተቋማት ቸልተኝነት፡ ዕቅዱን በባለቤትነት ያለመያዝ፥ ተጣድፎ ያለማጣደፍ፥ በዕለት ተዕለት ስራዎች መጠመድ፥ ማህበረሰቡን በብቃት ያለማሳተፍና በበቂ ያለማነቃነቅ እንዲሁም ከረጅሙ ግብ አንፃር አለመንቀሳቀስ ይስተዋላል።

በዚህ ረገድ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ ትክክለኛ አቅጣጫን የተከተለ ቢሆንም ብዙ ይቀረዋል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ስራቸው ሁሉ ተማሪንና ህብረተሰቡን ማዕከል ያደረገ እንዲሆን የሚያደርጉት ጥረት ውሱን ነው፡፡ በአንዳንድ ተቋማትም ተማሪን ማዕከል ከማድረግ ተቋሙን መዝጋት የሚመረጥበት፥ መምህራኑ የበላይ፥ የዕውቀት ምንጭና አስተሳሳፊ፥ እንዲሁም ብቸኛ የምርምር ኃይሎች የሆኑበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ የሚያስለጥኑት ተማሪ ነገ የሥራ ፈጣሪ፥ የሃገር ችግር ፈቺ ተመራማሪ፥ በየሙያ መስኩ የሚሰማራ ዜጋና የወደፊቱ መሪ መሆኑ በቂ ግንዛቤ የተያዘበት አይመስልም፡፡ በዚህም ምክንያት ከሥር ኮትኩቶ ተተኪ ትውልድ የማዘጋጀቱ ኃላፊነት እየተዘነጋ በሙያው "ብቸኛ" የመባል አዝማሚያ በብዛት ይታያል፡፡

ሥርዓተ ትምህርቶች ከሃገራዊ ሁኔታ ጋር የተገናዘቡ፥ ተገቢና ወቅታዊ የመሆን አስፈላጊነታቸው ወደጎን እየተተወ በመምህራኑ ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ፥ ከሃገራዊ ሁኔታዎች ይልቅ ለአውሮፓና አሜሪካ ሁኔታዎች የሚያዘጋጁ፥ ተግባር ተኮር ከመሆን በንድፈ ሃሣብ ላይ ያተኮሩ ወዘተ. መሆናቸውን ለማሻሻል ጥረት መደረግ ይኖርበታል፡፡

በየደረጃው ያለው የተቋም አመራር (ቦርድ፥ ፕሬዚዳንት፣ ዲን፥ ትምህርት ክፍል ኃላፊ ወዘተ.) የተቋሙን ህብረተሰብና በተለይም ተማሪውን ያሳተፈ እንቅስቃሴ የማድረግ አካሄድ በጣም ውሱን ነው፡፡ ይህም የዲሞክራሲ ሥርዓትን ለመገንባት ብሎም ግልጽና አሳታፊ የሆነ አሰራር የመዘርጋትን፣ የተጠያቂነት አግባብን የማወቅና የማሳወቅን፥ የግልና የጋራ ጥረትን የማቀናጀት፥ የመጠቀምና ዕቅውና የመስጠትን ወዘተ ባህል ለማጎልበት የሚደረገውን እንቅስቃሴ ውሱንነት ያመለክታል፡፡

ተቋማት ባሉባቸው አካባቢዎች የሚኖረውን ህብረተሰብ በብቃት ለማገልገል፥ ችግሩን የሚፈቱ ምርምሮች ላይ ትኩረት በመስጠት ለመንቀሳቀስ፥ በጋራ የልማት ስራዎች ላይ ለመሳተፍ፥ ወዘተ. የሚያደርጓቸው ጥረቶች ውስን ናቸው፡፡ በእርግጥ አንዳንድ ተቋማት ከአካባቢው ህብረተሰብ፥ መስተዳድርና ክልል መንግስታት ጋር ያላቸው ግንኙነት የተጠናከረና መልካም ውጤቶችን ያስመዘገበ ነው፡፡ በብዙዎቹ ተቋማት በኩል ግን አሁንም ራስን ከሌሎች ነጥሎ የመቀመጥና ኃላፊነት የለብኝም የማለት አዝማሚያዎች ይስተዋላል፡፡ ይህ በአፋጣኝ መስተካከል ያለበት ጉዳይ ነው፡፡

ስለዚህ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ማኅበረሰቡ ለልማቱና ለዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ፈጥነን መንቀሳቀስ፥ ገዢ የሆኑ ችግሮችንና ተግባራትን

በመለየትና በዕቅድ በመመራት ለለውጥ መነሳሳት በኃላፊነትና በባለቤትነት መድከም ይኖርብናል። ይህ ጥረትና ድካም ግን ከድህነት የመውጣት፣ የዲሞክራሲ ባህልን የመገንባትና በአጠቃላይ ውጤታማ የመሆን ራዕይና ግብ ይዞ መሆን አለበት።

## የማጣቀሻ ምንጮች:


የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን 1995
የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን 1995

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር 1995

የትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ስታቲስቲክስ ዓመታዊ አብስትራክት 1994

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግስት የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራቴጂና ፕሮግራሞች. 1994

**Higher Education in Developing Countries: Peril and Promise**. The World Bank, 2000.

**The State of the World's Children 2003**. Unicef, 2002

Unesco Insitute for Statistics. Unesco, 2002

**World Development Indicators Database**. The World Bank, 2002.

**World Development Report 1999-2000**. The World Bank, 2000.